## የተሰጠን፡ መንፈስ - ፍቅር

እግዚአብሔር፡ የሰጠን፡ የኃይል፤ የፍቅርና፡ ራስን፡ የመግዛት፡ መንፈስ፡ እንጂ፡ የፍረሃት፡ መንፈስ፡ አይደለም። ባለፈው፡ ሳምንት፡ የተሰጠን፡ መንፈስ፡ በውስጣችን፡ ታላቅ፡ ነገርን፡ የሚሰራ፡ ኃይል፡ እንደሆነ፡ አይተናል። ይህ፡ የኃይል፡ መንፈስ፡ የፍቅርም፡ መንፈስ፡ ነው። ፍቅር፡ ብርቱ፡ ነገር፡ ነው። መጽሓፍ፡ ቅዱስ፡ "ፍቅር፡ እንደ፡ ሞት፡ የበረታች፡ ናትና … ብዙ፡ ውኃ፡ ፍቅርን፡ ያጠፋት፡ ዘንድ፡ አይችልም" ይላል (መኃ 8፡ 6-7)። ስለ፡ ፍቅር፡ ሃያልነት፡ ብዙ፡ መጽሐፍት፡ ተጽፏል፤ ፍቅር፡ በብዙ፡ ዜማ፡ ተወድሷል፤ ፍቅርን፡ ለመግለጽም፡ ብዙ፡ ቀለም፡ ከሽራ፡ ተዋህድዋል። ነገር፡ ግን፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ የተገለጠበት፡ መንገድ፡ ከዚህ፡ ሁሉ፡ በላይ፡ ነው። የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ምክንያት፡ የሚፈልግ፡ ፍቅር፡ አይደለም። ገና፡ ሃጢያቶኞች፡ ሳለን፡ ክርስቶስ፡ ስለ፡ እኛ፡ በመሞቱ፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ለኛ፡ ተገልጧል። የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ሁሉን፡ አቀፍ፡ ነው። እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ ሁሉ፡ ይወዳል። ስለዚህ፡ ጉዳይ፡ መጽሐፍ፡ ሲናገር፡ "በእርሱ [በክርስቶስ] የሚያምን፡ ሁሉ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ እንዲኖረው፡ እንጂ፡ እንዳይጠፋ፡ እግዚአብሔር፡ አንድያ፡ ልጁን፡ እስከ፡ መስጠት፡ ድረስ፡ ዓለምን፡ እንዲሁ፡ ወዶአልና" ይላል (ዮሐ 3፡16)። የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ማንኛውንም፡ ሁኔታ፡ ሊሸፍን፡ የሚችል፡ ነው። ምንም፡ አይነት፡ ሰዎች፡ ብንሆን፤ በማንኛውም፡ መለኪያ፡ ልንወደድ፡ የማንችል፡ ብንሆንም፡ እንኳ፡ በክርስቶስ፡ ከተገለጠው፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ክልል፡ ልንወጣ፡ አንችልም። ለዚህ፡ ነው፡ የክርስቶስ፡ ፍቅር፡ በጥልቀቱ፡ በከፍታው፡ በስፋቱና፡ በርዝመቱ፡ ከመታወቅ፡ ያልፋል፡ የተባለው። የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ ወሰን፡ የሌለው፡ ፍቅር፡ ነው።

መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ስንቀበል፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ በልባችን፡ ፈሷል (ሮሜ 5፡ 5)። ይህ፡ ማለት፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋር፡ ባለን፡ ሕብረት፡ መሰረትና፡ ልክ፡ አስደናቂ፡ የሆነው፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ በሕይወታችና፡ በአገልግሎታችን፡ ይገለጻል፡ ማለት፡ ነው። ፍቅር፡ የክርስቲያን፡ መሰረታዊ፡ የሆነ፡ መገለጫ፡ ባህሪው፡ ነው። ለዚህ፡ ነው፡ ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ደቀ፡ መዛሙርቴ፡ እንደሆናችሁ፡ እርስ፡ በእርስ፡ ባላችሁ፡ ፍቅር፡ ትታወቃላችሁ፡ ያለው (ዬሐ 13፡ 35)። የቤተሰብ፡ መሰረት፡ ፍቅር፡ ነው። ልክ፡ በክርስቶስና፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ መካከል፡ ያለው፡ ግንኙነት፡ እራስን፡ በመስጠት፡ ፍቅር፡ ላይ፡ የተመሰረተ፡ እንደመሆኑ፡ በባልና፡ በሚስትም፡ መካከል፡ ያለው፡ ግንኙነት፡ መሰረቱ፡ ፍቅር፡ ነው። ፍቅር፡ ከሁሉ፡ የሚበልጥ፡ የአገልግሎት፡ መንገድ፡ ነው። በፍቅር፡ ያልሆነ፡ አገልግሎት፡ እግዚአብሔርን፡ ደስ፡ አያሰኘውም። ለዚህ፡ ጥሩ፡ ምሳሌ፡ የሚሆነን፡ ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከትንሳኤው፡ በኋላ፡ ከጴጥሮስ፡ ጋር፡ ያደረገው፡ ምልልስ፡ ነው። ጌታ፡ ጴጥሮስን፡ የአግልግሎት፡ ሃላፊነት፡ ከመስጠቱ፡ በፊት፡ ደጋግሞ፡ ትወደኛለህን፡ ሲለው፡ እንመለከታለን። የአግልግሎት፡ መሰረት፡ ለጌታ፡ ያለን፡ ፍቅር፡ ነው። ፍቅር፡ የማንነትና፡ የባህርይ፡ ጉዳይ፡ ስለሆነ፡ ለጌታ፡ ያለን፡ ፍቅር፡ ለሰዎች፡ ሁሉ፡ ፍቅር፡ እንዲኖረን፡ ያደርገናል። በውስጥ፡ ላሉት፡ እንራራለን። በውጭ፡ ላሉት፡ እንቅናለን። የተረዳነውንና፡ የተገለጠልንን፡ እውነት፡ እንኳ፡ በፍቅር፡ ካላካፈልነው፡ ፍይዳ፡ አይኖረውም።

ወገኖቼ፡ እግዚአብሔር፡ የሰጠን፡ የፍቅር፡ መንፈስ፡ ነው። ይህ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በውስጣችን፡ የሚያደርገው፡ ፍቅር፡ እግዚአብሔርን፡ የሚገልጽ፡ ፍቅር፡ ነው። ፍቅር፡ ይታገሣል፥ ቸርነትንም፡ ያደርጋል፤ አይቀናም፤ አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን፡ አያደርግም፥ የራሱንም፡ አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን፡ አይቆጥርም (1ቆሮ 13፡ 4-6)። የእግዚአብሔር፡ ባህርይ፡ ነጸብራቅ፡ የሆነው፡ ሕግም፡ የሚጠቀለለው፡ በፍቅር፡ ነው። ያውም፡ እግዚአብሔርን፡ በመውደድ፡ ሰዎችን፡ ሁሉ፡ መወደድ፡ ነው።